


ሚያዚያ 20 ቀን 2001 ዓ/ም

## ቀደም ሲል ከፋኝ በመባል በሚታወቀው እንቅስቃሴ ውስጥ የቁፋ ሁመራና የወልቃይት ጦር አዛዥ የነበሩ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባርን ተቀላቀሉ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን ጭካኔ የተሞላበት የዘረኛ ሥርአት ለማስወገድ የሚያካሂደው የትጥቅ ትግል ሕዝባዊ መሰረት ያለው በመሆኑ ከቀን ወደቀን ግንባሩን የሚቀላቀሉ የኢትዮጵያውያኖች ቁጥር እየጨመረ ይገኛል።

ከኢሕአግ ምስረታ በፊት ከፋኝ በመባል በሚታወቀው የትጥቅ ትግል ውስጥ ሰራዊቱን በመምራት፤ ከፍተኛ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ ሁለት ግለሰበች ግንባሩን በመጋቢት ወር 2001 ዓ/ም ላይ ተቀላቀሉ።

1ኛ አቶ ልኡል ገብረመስቀል ቢያድግልኝ በከፋኝ እንቅስቃሴ የቁፋ ሁመራ የጦር አዛዥ በመሆን ከ1979 ዓ/ም እስከ 1984 ዓ/ም ወያኔን በመታገል ከፍተኛ ወታደራዊ ድሎችን ያስመዘገቡ ሲሆን በወቅቱ ወያኔ በሽምግልናና በምህረት ወደሰላመዊ ኑሮ እንዲመለሱ ካግባበቸው በኋላ የሞት ፍርድ ፈርዶባቸው ነበር። ሆኖም የአለም አቀፍ ቀይመስቀል በጉዳዩ ጣልቃ በመግባት የፖለቲካ እስረኛ መሆናቸውን እውቅና በመስጠቱ የሞት ፍርዱ ወደ 20 አመት አስራት ተለውጦ ከአስራ አምስተ አመት እስራት በኋላ በአመክሮ የተለቀቁ ሲሆን፤ 14 አመቱን የእስራት ጊዜ ያሳለፉት በዘረኛውና አረመኔው የወያኔ ቡድን እጆቻቸው በሰንሰለት በየእለቱ እንዲታሰሩ በማድረግ ነበር።

2ኛ አቶ ሽባባው አበበ ጎነጠ በከፋኝ እንቅስቃሴ የወልቃይት ጦር አዛዥ በመሆን ከ1978 ዓ/ም እስከ 1985 ዓ/ም መጠነ ሰፊ የሆኑ ወታደራዊ ድሎችን ያስመዘገቡና በወቅቱ የተደረገላቸውን ምህረት በመጠቀም ወደሰላመዊ ኑሮም ከተመለሱም በኋላ የኢሕአግን ድርጅታዊ መዋቅር በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በመዘርጋት ከፍተኛ የማደራጀት ስራ አከናውነዋል።

እነኚህ ጀግኖች አርበኞች በከተማ ውስጥ የነበራቸውን የማደራጀት ተግባራቶችን ሲያካሂዱ ቆይተው፤ በመጋቢት ወር 2001 ዓ/ም ከአዲስ አበባ በመነሳት፤ ዛሬም እንደቀድሞው ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ለመነጋገር ግንባሩን ተቀላቅለዋል።

በቅርቡ በጀመረውና ወደኢትዮጵያ በመተላለፍ ላይ በሚገኘው የአርበኞች ድምጽ ሬድዮናችን ላይ
የሰጡትን ቃለ መጠይቅ ለአድማጭ እንደምናቀርብ በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እንወዳለን።

**አንድነት ሃይል ነው**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር!**

Email: info@eppfonline.org:    Website: www.eppfonline.org